# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 138 ታህሳስ 28 ቀን 2003 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የትግራዩ ገዥ ጉጅሌ በዘረፋ ባሰባሰበው የኢትዮጵያ ህዝብ ሃብት ደረቱ ተነፍቷል። በቅኝ ግዛት ዘመን እንኳን ከእጁ ያልወጣውን የኢትዮጵያን መሬት ዛሬ ለባዕዳን እየሸጠ የወያኔን ባለስልጣናት ገንዘብ የውጭ ሃገር ባንኮች እያስጨነቀ ባለበት ሁኔታ "የውጭ ኢንቬስተር አመጣሁላችሁ እልል በሉ" ይለናል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ

## በሙስና ምክንያት የታሰሩ የኦሮምያ ክልል ባለስልጣናት በድብቅ ተፈተው እየተሾሙ እንደሆነ ታወቀ

የወያኔ አገዛዝ ከመሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ በሙስና ተዘፍቀዋል ብሎ ያሰራቸውን የኦሮምያ ክልል ባለስልጣናት በጎን እየለቀቀና እየሾመ መሆኑን ከአዲስ አበባ የደረሱን ዘገባዎች አመልክተዋል።

አገዛዙ መሬት ህገ ወጥ በሆነ መንገድ መርተዋል፣ እንዲሸጥም ፈቅደዋል ብሎ ያላቸውን የሰበታ ከተማ ባለስልጣናት እንዳሰረ ከጥቂት ሳምንታት በፊት መዘገባችን ይታወሳል። ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ከስልጣኑ የወረደው የሰበታ ከተማ ባለስልጣንም ወደሌላ ቢሮ ተወስዶ መሾሙን ገልጸናል። በዚህ ሳምንት የደረሰን ዘገባ እንደሚያመለክተው፤ ይህ ክስተት በአካባቢው ባሉ ሌሎች ከተሞችም ሳይገታ እንደቀጠለ ነው።

የዘገባ ምንጮቻችን እንደገለጹት፥ በከተማ ደረጃ ያሉት ባለስልጣናት የሚሰሩት በከፍተኛ ስልጣን ላይ ካሉ የአገዛዙ ባለስልጣናት ጋር በመመሳጠር እና በሙስና ያገኙትን ገንዘብ በማካፈል ነው። ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ መሬት በመመራት እና በመሸጥ ድርጊቱም እንደ አዜብ መስፍን እና አባ ዱላ ገመዳ ያሉት ሙሉ በሙሉ ተሳታፊዎች ናቸው። ከዚህ አኳያም፥ የቀድሞው የሰበታ ከንቲባ፥ ለባለስልጣናቱ የፈለጉትን ያህል መሬት ቢሰጣቸውም በቃኝ አያውቁም ብሎ ሲያማርር መሰማቱን ለግለሰቡ ቅርብ የሆኑ ምንጭ ለዘጋቢያችን ተናግረዋል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ሪፖርተር ጋዜጣን ያናገሩት ዶ/ር መረራ ጉዲና ከሙስና ጋር በተያያዘ እየተካሄደ ባለው እስር ዋና ዋናዎቹ ተሳታፊዎች እንዳልተነኩ ገልጸዋል። ከታች ያሉት ባለስልጣናት ደግሞ በአንድ ጎን እየታሰሩ እና የበርካታ አመታት ፍርድ እንደተፈረደባቸው በመገናኛ ብዙሃን እየተነገረ፣ በሌላ ጎን ግን በበላዮቻቸው በኩል በሚደረግ ግፊት እየተለቀቁ እንደሆነም ዶ/ሩ መስክረዋል።

## የአባ ዱላ ገመዳ የቀኝ እጅ የምትባል መሃንዲስ ቤት ከምር ብር መገኘቱን መረጃ አመልክቷል

"ሚሚ" በሚል ቅጽል ስም የምትታወቀው መሃንዲስ በሰበታ ከተማ የመሬት አስተዳደር ጉዳይ ላይ "ፈላጭ ቆራጭ" እንደነበረች ምንጮቻችን ገልጸዋል።

ግለሰቧ ለአዜብ መስፍን ከፍተኛ መጠን ያለው መሬት የሰጠው የመሬት አስተዳደር ቢሮ ባልደረባ ከመሆኗም ባሻገር፣ የአባ ዱላ ገመዳ የቅርብ ሰው እና ስራ አስፈጻሚ መሆኗን ለከተማው ባለስልጣናት ቅርበት ያላቸው ግለሰብ ለሪፖርተራችን ነግረዋል። ይሁን እንጂ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ሙስናን በመዋጋት ስም አንዳንድ አገልጋዮቹን ማሰር ሲጀምር ከተያዙት ውስጥ አንዷ ሆናለች። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ጥቃት የተከፈተበት የንግድ ማህበረሰብ በከፍተኛ ሽብር ላይ ነው

የዘረኛው እና አምባገነናዊው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከአንድ ዘር በተውጣጡ ጥቂት ምርጦች ሙሉ ቁጥጥር ስር ለማዋል ካለው ፍላጎት የተነሳ የከፈተባቸው ጥቃት የንግዱን ማህበረሰብ አባላት ከፍተኛ ሽብር ውስጥ እንደከተተ ዘገባዎች እያመለከቱ ነው።

የኢትዮጵያ የንግድ ምክር ቤት ፕሬዚደንት ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ እሁድ እለት ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፣ ባሁኑ ሰዓት በነጋዴዎች ላይ እየተወሰዱ ያሉትን እርምጃዎች "አስፈሪ፣ አስደንጋጭ እና አሸባሪ" ሲሉ ገልጸዋል። አቶ ኢየሱስ ብዙ ነጋዴዎች ስልክ እየደወሉ ስጋታቸውን እንደሚገልጹላቸው እና አንዳንዶችም ከአገር መውጣት ይሻላቸው እንደሆነ ምክር እንደሚጠይቁ ለሪፖርተር ነግረዋል።

ህግ በማስከበር ስም እየተካሄደ ያለው እርምጃ የተዛባ መሆኑን የሚገልጹት የንግድ ማህበረሰብ መሪ፤ ጥፋተኞች እየታለፉ ህግ ያከበሩት የሚታሰሩበት ሁኔታ እንደተስፋፋ አስረድተዋል። ጨምረውም፥ ምንም እንኳ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ስራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ የመጡ ዜጎች በፌዴራል ፖሊስ ጥቃት እየተፈጸመባቸው ነው

ስራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ የመጡ ዜጎች ለችጋር እና እንግልት መዳረጋቸው ሳያንስ በትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ፌዴራል ፖሊስ ጥቃት እየተፈጸመባቸው እንደሆነ ከመዲናይቱ የደረሰን ዘገባ አሳይቷል።

የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ እንደገለጸው፥ ባለፈው አርብ በተለምዶ መገናኛ፣ ሜክሲኮ እና አራት ኪሎ ተብለው በሚጠሩት አካባቢዎች የፌዴራል ፖሊስ ሱቅ በደረቴዎችን ዘርፏል። አካባቢው የጦር ቀጠና እስኪመስል የፖሊስ ሃይሉ በሙሉ ትጥቅ ወጥቶ ሱቅ በደረቴዎቹን እንደከበበ የታወቀ ሲሆን፤ ንብረታቸውን የተቀሙት የመንገድ ላይ ነጋዴዎች ሲያለቅሱ ተስተውለዋል።

በስፍራው ተገኝቶ የአይን እማኝ የነበረውን ዘጋቢያችንን ያናገሩት ሰለባዎች፥ ተስፋ ቢስ እንደሆኑ እና አንዳች እንደሌላቸው በምሬት ተናግረዋል። በርካቶቹ ቤተሰቦቻቸው ከግብርና የሚያገኙት ገቢ በቂ ስላልሆነ እራሳቸውንም ለማገረፍ እና ወላጆቻቸውን ለመርዳት ሲሉ ከክፍለ ሃገራት የመጡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ አስከፊ ደረጃ ላይ የደረሰ የከተማ ውስጥ ድህነት፤ የኑሮ ውድነት፤ የመሬት እና የንብረት ቅሚያ፤ ረሃብ እና ችጋር ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ተባብሰዋል። መንግስት ሰራተኞች፣ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች እና ስራ አጦች ሁሉ በምሬት የተጎዱ ሲሆን፤ በርካቶቹም ለሚደርስባቸው ችግር ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ተጠያቂ ነው ብለው እንደሚያምኑ የህዝብ አስተያየት አሰሳዎች ያመለክታሉ።

## የውሃ ዋጋ በመቶ እጅ ጨመረ

የኢትዮጵያን ህዝብ የተጋፈጠው የኑሮ ውድነት እና ዘረፋ ሳይገታ ቀጥሎ፣ ከሰሞኑ በመለስ ዜናዊ ቁጥጥር ስር የሚገኘው የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር በውሃ ዋጋ ላይ ጭማሪ ማድረጉን አስታውቋል።

ከዚህ ቀደም ሶስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም የነበረው አንድ ሜትር ኪዩብ ውሃ በእጥፍ ዋጋ ጨምሮ ሰባት ብር እንደሚሆን ተገልጿል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፥ የውሃ አገልግሎት እንደ መብራት ሁሉ ህዝቡን ሲያማርር እንደቆየ መዘገባችን ይታወሳል። በአዲስ አበባ ከተማ አንዳንድ አካባቢዎች፣ የውሃ አገልግሎት በሁለት ሳምንት አንዴ ብቻ እንደሚገኝ ነዋሪዎች ይናገራሉ።

የዋጋ ጭማሪውን አስመልክተው ዘጋቢያችንን ያናገሩት ዜጎች ከወዲሁ ስጋታቸውን የገለጹ ሲሆን "ውሃ ሁልጊዜ ባይመጣም እንኳ ከሌላ ነገር ጋር ሲነጻጸር ደህና ዋጋ ያለው እሱ ብቻ ነበር" ያሉን አንዲት እናት፤ "እሷንም ወሰዱብን" ሲሉ አማረዋል።

## ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ መዋቅራዊ ዘረኛነትን ማጠናከሩን እንደገፉበት ነው

የኢትዮጵያን የመንግስት ስልጣን በጉልበት ተቆጣጥሮ ያለው የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ፤ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ያሰፈነውን መዋቅራዊ ዘረኛነት በማናለብኝነት ማስፋፋቱን እንደቀጠለ ነው።

ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ የተመረጡ የትግራይ ተወላጆችን ቁልፍ በሆኑ የመንግስት የስልጣን መቀመጫዎች ላይ ማስቀመጡን የቀጠለ ሲሆን፤ ባለፈው ሳምንት መድህን ኪሮስ ገብረእግዚአብሔር የተባለውን የቀድሞ የህወሃት ታጋይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚደንት አድርጎ ሹሟል።

ግለሰቡ ከበርካታ ወራት በፊት ስራውን ለቆ ሌላ ሹመት የተሰጠውን መንበረጸሃይ ታደሰን የሚተካ ነው። መንበረጸሃይ ታደሰ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውስጥ የመለስ ዜናዊ ስራ አስፈጻሚ እንደሆነ በቅርብ የሚያውቁት ይናገራሉ። በተለይ ከፖለቲካ እና ከወያኔ የንግድ እንቅስቃሴዎች ጋር ለተያያዙ የፍርድ ሂደቶች ከዳኞች በስተጀርባ ሆኖ ውሳኔዎችን እንደሚያስተላልፍ አንድ ዳኛ መናገራቸው ይታወሳል።

ከሌሎች ዘውጌ ማህበረሰባት የመጡ ግለሰቦችን ለይስሙላ መሾም እና በምክትልነት ግን እውነተኛውን ስልጣን የሚይዙትን የትግራይ ተወላጆች ማስቀመጥ በዘረኛው አገዛዝ ዘንድ የተለመደ አሰራር መሆኑ ይታወቃል።

## ደርጎችን እንደ አጥንት፤ ህዝብን እንደውሻ! አይ ፎርሙላ!!!

የትግራዩ ገዥ ጉጅሌ በዘረፋ ባሰባሰበው የኢትዮጵያ ህዝብ ሃብት ደረቱ ተነፍቷል፤ ቁጥጥር የለሽ ስልጣን እብሪቱን ገደብ አሳጥቶቷል። ስልጣንና ሃብት ተሳክረውበታል፤ አስክረውታልም። አሁንማ ብሶበት ወደ አጠቃላይ እብደት እያመራ ነው።

የወያኔ እብደት ዋነኛ ማረጋገጫ ራሱ ጠፍጥፎ የሰራውን ጣኦት ራሱ ተንበርክኮ ከማምለክ አልፎ እኛም እናመልክለት ዘንድ መፈለጉ ነው። ራሱ የፈጠራቸው ውሸቶች እውነት እየመሰሉት ሌሎችም እንዲያምኑለት የሚያደርገው ጥረት ራሱ የሰራውን ጣኦት አምላክ ነው ብሎ ከመስገድ የተሻለ ምን አቻ ገላጭ ይገኝለታል? የወያኔ ጣኦትን የማምለክ ተግባር ምን እንደሚመስል አንዳንድ ምሳሌዎችን እንጥቀስ።

- የትግራዩ ገዥ ጉጅሌ የዘረጋው በዓለም በኋላ ቀርነቱና በክፋቱ ወደር ያልተገኘለትን አምባገነናዊ ስርአት "ዲሞክራሲ ነው" ይለናል። የውሸት ምርጫዎች መኖራቸው፤ አንዳች ዋጋ የሌለው ፓርላማ ተብዬ ሸንጎ በሳምንት አንዴ ተሰብስቦ የሚያጨበጭብ መሆኑ፤ ሥራ ላይ ውሎ የማያውቅ ህገ መንግሥት መፃፉ ለጉጅሌው የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ማስረጃዎቹ ናቸው። ለውሸት ምርጫ፣ ለእርባና ቢስ ፓርላማ እና ለፋይዳ ቢስ ህገመንግስት እየሰገደ እኛንም ስገዱ ይለናል። ለእኛ ይህ ሰው ሰራሽ ጣኦትን እንደማምለክ ነው።
- በጥቂት የትግራይ ዘረኞች እጅ የኢትዮጵያ ህዝብ መረገጡና መዘረፉ የብሄር ብሄረሰቦች መብት መከበር ውጤት ነው ይለናል። በመላው ሃገሪቱ ዜጎችን በዘራቸው እየለየ እያሳደደ፣ እያሰረ፣ ሰቆቃ እየፈጸመ፣ በጅምላ እየገደለና እያዋረደ የብሄረሰቦች መብት አስከብሪያለሁ ይለናል።
- ሃገራዊ ክህደትን የሃገራዊ ጥቅምና ደህነነት ቅብ ቀብቶ "ማን እንደኔ ለኢትዮጵያ?" እያለ ይሸልልብናል። ወያኔ ስልጣን ላይ ለመሰንበትና የሀገሪቱን ሃብት ለመዝረፍ ሲል የወሰዳቸውን የኢትዮጵያን ብሄራዊ ደህነትና ጥቅም የሚጎዱ በርካታ እርምጃዎች "ለሰላም ስል፣ ለበጎ ጉርብትና ስል የወሰደኳቸው ናቸው" በማለት ላሞኛችሁ ይለናል።
- ጥቂት በዘራቸው ያሰባሰባቸው ዘረኞች ህይወት የምድር ላይ ገነት መምሰሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮ መሻሻል ምልክት ነው ይለናል። የአብዛኛውን ህዝብ ህይወት ወደ ሲኦል ቀይሮ፤ አብዛኛው ህዝብ ያለፈረንጆች እርዳታ ህይወቱን ማቆየት ከማይችልበት የሞት አፋፍ ላይ አድርሶ፤ የኢትዮጵያ እናቶች ልጆቻቸውን በፈረቃ የሚመግቡበት የችጋር ዘመን በሃገር አንግሶ እያለ "ሃገር እየለማና እየበለጸገ ነው" ይለናል።
- የመንግስት ሰራተኛው በኑሮ ውድነት ከወር ወር መድረስ አቅቶት የተፈጠረበትን ቀን በሚራገምበት ሁኔታ እያለ፤ ወያኔ ለዘረጋው በልቶ ለማይጠግበው ጆሮ ጠቢ ሰላይና ወታደር እንዲሁም ለቢሮክራሲው የሚያስፈልገውን የገንዘብ አቅርቦት ለመሸፈን ነጋዴውን እንደላም እያለበ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት በአምስት ዓመታት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገሮች ተርታ ትደርሳላችሁ እያለ ያላግጥብናል።
- የወያኔ ዘረኛ ጉጅሌ ልጆች በአሜሪካና አውሮፓ በአመት አምሳ ሺህ ዶላር በሚከፈልባቸው ትምህርት ቤቶች እየተማሩ በባዶ ሆዱ ያለበቂ የመማሪያ ግብዓትና አስተማሪ እንደ ርካሽ እቃ እያመረተ ሜዳ ላይ የሚዘረግፈውን ወጣት በትምህርት እድገት ማስረጃነት ተቀበሉልኝ ይላል።
- በቅኝ ግዛት ዘመን እንኳን ከእጁ ያልወጣውን የኢትዮጵያን መሬት ዛሬ ለባዕዳን እየሸጠ የወያኔን ባለስልጣናት ገንዘብ የውጭ ሃገር ባንኮች እያስጨነቀ ባለበት ሁኔታ "የውጭ ኢንቬስተር አመጣሁላችሁ እልል በሉ" ይለናል።

እነዚህንና የመሳሰሉትን ነው የወያኔ ሰው ሰራሽ ጣኦት ባዕድ አምልኮት ያልነው።
የወያኔ የተሃድሶ ተረት ሙቶ በቦታው የተተካው ሌጣ የትራንስፎርሜሽን ዝማሬ አድማጭ ባጣበት፤ ወያኔ ከሃገር ወዳዱ፣ ከወጣቱ ከሲቪል ማህበረሰቡ፣ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከሁሉም የሃገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦች ጋር ተፋጦ በቆመበት፤ በውጭ የሚገኙ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ወያኔ በፈጸመው የዘር ማጥፋት፣ በጦርና በሰብአዊነት ላይ በፈጸመው ወንጀል ይጠየቅ የሚለው ጥሪያቸው በተጠናከረበት ሁኔታ የህዝብን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ሌላ አይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛችሁ የሚል አጀንዳ ይዞ መጥቷል።

ወያኔ በመሳሪያነት የሚጠቀምባቸው የእምነት ተቋማትን ቀስቅሶ "የሃይማኖት አባቶች በቀድሞ የደርግ ባለስልጣናት ላይ የይቅርታ ጥያቄ እንዲደረግ ጥያቄ አቀረቡ" የሚል የአጀንዳ አጥንት ወርውሮልናል። አንዳንድ የዋሆች ይህንን የወያኔን አጥንት ይዘው መራኮት ጀምረዋል። ይፈቱ አይፈቱ፤ ምህረት ይደረግላቸው አይደረግላቸው በሚል ክርክር ጎራ ይዘው ይነታረካሉ። ወያኔ የፈለገው ይህንኑ ነው።

በገፍ እየታሰረን፣ እየተሰደድን፣ በጥይትና በረሃብ እያለቅን፤ በወያኔ ዘረኞች ጥቃትና ውርደት እየተሰነዘረብን እያለ ወያኔ "ህዝብ ውሻ ነውና አጥንት ልጣልለትና በርሱ ሲራኮት አፈናየን፣ ዘረፋዬን፣ ዘረኛ ማነቆየን ላጠናክር" ብሎ አቅዶ በቆፈረው ማቅ ውስጥ ገብተን የምንዳክረው ለምንድነው? በእውነቱ ዛሬ ይህ የእኛ አጀንዳ ነውን?

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሃገራችንና ህዝባችን የሚገኙበት እጅግ አሳዛኝና አዋራጅ ሁኔታ የሚያሳስባቸው ሃይሎች በእንዲህ አይነቱ የወያኔ ርካሽ ወጥመድ ውስጥ መውደቅ የለባቸውም ብሎ ያምናል። ወያኔ ስለቀድሞ የደርግ አባላት የፈለገውን አርኬስትራ ቢያዘፍን፤ እኛ አይኖቻችንንና ጆሮዎቻችንን ከሃገር አውዳሚው፣ ዘረኛው፣ ዘራፊው እና ግፈኛው ወያኔ ላይ መንቀል የለብንም። እኛን በእጅጉ የሚያስጨንቀን ዛሬ በሃገራችን ምድር በዘሩ እየተለየ የሚቀጠቀጠው፣ የሚታሰረው፣ ሃገር ጥሎ እንዲሰደድ የሚገደደውና የሚገደለው ህዝባችን እጣ ፈንታ ነው። እኛን የሚያሳስበን በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ በማይታወቅ ደረጃ እየተዘረፈ ያለ ሃብት ነው። እኛን የሚያሳስበን የወያኔ ሃገርን ለባእዳን የመሸጥ ድርጊት ነው። እያስጨነቀን ያለው የወጣቱ፣ የተማሪው፣ የመንግስት ሰራተኛው፣ የነጋዴውና የገበሬው በሃገሩ ላይ ተስፋ እንዲያጣ እየተደረገ ያለበት ሁኔታ ነው።

እኛ ወያኔ የሚባል ይቅርታ አድራጊና ምህረት ሰጭ አናውቅም። የቤተ አምልኮት ተቋማቱ መሪዎች ወያኔ በሰራው ወንጀል ተጠያቂ የማድረግ ሃይማኖታዊ ግዴታችሁን መወጣት ሲገባችሁ ይብሱኑ እሱኑ እንደ ብጹእ በመቁጠር ምህረት አድራጊ አድርጋችሁ በማቅረባችሁ እየታዘብናችሁ ትኩረታችን ወያኔን በማስወገድ ስራ ላይ መሆኑን እንነግራችኋለን። የደረቀ አጥንት እየወረወሩልን ሥራ የማስፈታት ፎርሙላ ከእንግዲህ አይሰራም ብለናል።

## በነጋዴዎች ላይ የሚደረገው ጥቃት ቀጥሏል

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢትዮጵያ ነጋዴዎች ላይ የሚያደርገውን ጥቃት ቀጥሏል፤ ትናንሽ የንግድ ተቋማት ሳይቀሩ በአስርተ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር በውዝፍ ግብር እንዲከፍሉ እየታዘዙ ነው።

በአዲስ አበባ የሚገኘው ታዋቂው ባምቢስ መደብር ዘጠና አንድ ሚሊዮን ብር ውዝፍ ግብር፣ ወለድ እና ቅጣት እንዲከፍል የሚያዝ ደብዳቤ በዚህ ወር አጋማሽ ላይ እንደደረሰው አዲስ ፎርቹን የተባለው የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ዘግቧል። ባምቢስ ሲማስ የተባሉት እና የመደብሩ ባለቤት የሆኑት የሰማንያ አመት አዛውንት፣ የሂሳብ አወራራጆች ወይም አካውንታቶች ቀጥረው ስለሚያሰሩ ይህ ሁሉ ገንዘብ እንዴት እንዳልተከፈለ እንደማያውቁ በመጥቀስ፤ የገቢ ባለስልጣን የተጣለባቸውን ቅጣት ለመክፈል ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጣቸው እና ወለዱን ይቅር እንዲላቸው ተማጽነዋል። ይሁን እንጂ ባለስልጣኑ አቤቱታቸውን ውድቅ አድርጎታል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር የነበሩት ዶ/ር ታደሰ ብሩ ማክሰኞ እለት ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ቃለ መጠይቅ፥ እየተካሄደ ያለው "የህግ ማስከበር ጉዳይ ሳይሆን ባጠቃላይ ህብረተሰቡን ለመቆጣጠር የሚደረግ እርምጃ ነው" ብለዋል። ዶ/ር ታደሰ ጨምረውም፥ የንግዱ ማህበረሰብ ይህ አይነቱ ጥቃት እየቀጠለ ብቻ እንደሚሄድ ተረድቶ ይህንን ለማስቆም ስርአቱን ለመቀየር መጣር ይኖርበታል፤ ለነጻነት በሚደረገው ትግል ግንባር ቀደም ተዋናይ ሆኖ መሳተፍ አለበት ሲሉ መክረዋል።

## የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የፈረንጆቹን አዲስ አመት በማስመልከት መግለጫ አወጣ

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) የፈረንጆቹን አዲስ አመት በማስመልከት የእንኳን አደረሳችሁ መልክት አስተላልፏል፣ ለተከታዮቹ እና ለኦሮሞ ህዝብም የትግል ጥሪ አቅርቧል።

ኦነግ ባወጣው በዚሁ መግለጫ፥ የጥር ወር በኦሮሞ የትግል ታሪክ ውስጥ የሚታወስበትን ምክንያት ሲያስረዳ፣ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1980 በዚህ ወር የደርግ አገዛዝ ሊያጠፋው ተነስቶ ከፍተኛ ጥቃት ፈጽሞበት የነበረ ቢሆንም፤ ድርጅቱ ያንን ተቋቁሞ ማለፉ በአባላቱ እና በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ልዩ በሆነ ሁኔታ መታሰቡ ነው ብሏል።

ግንባሩ ያለፈባቸውን የትግል ምእራፎች እና እክሎች ካስታወሰ በኋላ፣ ለሚቀጥለው አመት ሊሰራቸው የተዘጋጀውን ተግባራት ዘርዝሯል። ከነዚህም ውስጥ የኦሮሞን ህዝብ ትግል አንድ ለማድረግ የተገባውን ቃል ከግብ ማድረስ፣ ወያኔን ዋና ኢላማ አድርጎ መነሳት እና ከሌሎች ህዝቦች እና ድርጅቶች ጋር ትብብር ለመፍጠር መስራት የሚሉት ይገኙበታል።

በተጨማሪም፥ "በጠላት ቀንበር ስር የምትገኘው የኦሮሞ ህዝብ ሆይ፤ ከቀዬህ ተነቅለህ በጎረቤት አገራት ሊነገር የማይችል መከራ እየደረሰብህ ላለኸው እና አምልጠህ ወደ ሩቅ አገር ለተሰደድከው፤ ትግልህን በሚፈሩ ሃይሎች እና በጠላት ሳትዘናጋ የሚጠበቅብህን ለመወጣት እንድትነሳ ጥሪ እናቀርባለን" ሲል መግለጫው መልክት አስተላልፏል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## አገር የማዳን ቀን ዛሬ ነው

ከሃያ አመት በኋላ ይመስለኛል፤ ወደ 2023 አካባቢ። በፈረንጆቹ ፊልም እንደሚያሳዩት በ"ታይም ማሺን" ወይም የጊዜ ማሽን አስርተ አመታትን ዘልዬ እዛ ደርሻለሁ። ከበርካታ አመታት በኋላ የትውልድ ከተማዬን ልጎበኝ መመለሴ ነው። እኔ ጥያት ስወጣ ከተማ እንኳ ለመባል የማትበቃው መንደር ፍጹም ተለዋውጣ ነበር።

በምኖርበት የምእራብ አገር የማያቸውን ከተሞች መስላለች። እንዳውም ያሉባት ህንጻዎች አዳዲስ እና የሚያማምሩ ከመሆናቸው የተነሳ በውበት በልጣቸዋለች። "እንዴ! እውነትም ወያኔዎች እንደሚሉት አገሪቱ አድጋለች ማለት ነው!" ብዬ ተገረምኩ። "ይሄ ጥሩ ነገር ነው" ብዬም ለራሴ ነገርኩ።

ከወላጆቼ ቤት በረንዳ ላይ ቆሜ በትውልድ ከተማዬ አዲስ ውበት ስደመም፣ የድሮ ጓደኞቼ በመንገድ ላይ ሲያልፉ አያቸዋለሁ። እነሱ ግን የከተማችንን አዲስ ውበት አይጋሩም። ምን የመሰሉ ሽበላዎች እንደነበሩ የማስታውሳቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጓደኞቼ ፊታቸው በቡጉር ተሸፍኖ ንጹህ ቆዳ የለበትም። ጠቋቁረዋል። ፈገግታም አይታይባቸውም። "ምን ነክቷቸው ነው? በዙሪያቸው ያለው ሁሉ ጥሩ ነገር ነው።" ብዬ ለራሴ ሳስን ተሰማኝ።

ምሽት ላይ ጓደኞቼ መጥተው ሲኒማ እንይ በሚል ከቤት ወሰዱኝ። ሲኒማ ቤቱ ያለው እቤታችን አካባቢ ባለ እና ውበቱ ሲያስደምመኝ ከቆየ ህንጻ ውስጥ ነው። ውስጥ ለመግባት እና ለማየት ጓጉቻለሁ። ስገባ ግን ያየሁትን ነገር ለማመን አልቻልኩም። አልቋል ተብሎ ከውስጡ የንግድ ቤቶች የሰፈሩበት እና ከውጪ ውበቱ ደምቆ የሚታየው ህንጻ ውስጡ ሌላ ታሪክ ነው።

ተቦክቶ ጥቅም ላይ ሳይውል በመቅረቱ በየቦታው ፈሳስሶ የቀረ ሲሚንቶ፣ የተሰበሩ መሰላሎች፣ የተቆራረጡ ብረቶች እና እዚህም እዚያም የተጋደሙ የግንባታ እቃዎች አሉ። ህንጻው ፎቆች አሉት። ውስጥ ሲገባ ግን ፎቁ እንደ ቀፎ ክፍት ነው። ከታች ወደላይ የሚያስወጣ ደረጃ አለ፤ አንዱን ፎቅ ከሌላው የሚለይ ወለል ግን አልተሰራም። በወለሉ ቦታ ከአንድ ጎን ወደ ሌላ የተወጠረ መረብ አለ። አወጣጠሩም ሁሉ ዝም ብሎ በግዴለሽነት የተሰራ ይመስላል።

ታዲያ ሲኒማ የምናይባቸው ክፍሎች ሁለተኛው ፎቅ ላይ እንደሆኑ ይነገረናል። እኔ የማየውን ነገር ማመን አቅቶኝ ፈጥጫለሁ። ጓደኞቼን ተከትዬ ደረጃውን ወጣሁ። መረቡ ጋ ስንደርስ ግን ብረግጠው እና ቢቀረጥ ወድቄ መፈጥፈጤ ነው ብዬ ፈራሁ። ከደረጃው ዳር ያለውን ሃዲድ የሙጥኝ ይዤ በፍጹም መረቡን አልረግጥም አልኩ። የሲኒማ ቤቱ ሰራተኞች ግን እንደኔ ላለው ሰው ትእግስት ያላቸው አለመሰሉም። አመናጭቀው ገፍተው መረቡ ላይ ጣሉኝ።

ከዛ በኋላ ሲኒማ ቤቱ ውስጥ የተከሰተውን ነገር አላስታውሰውም፤ ወይም ህልሜ በቀጥታ ወደሌላ ቦታ ወሰደኝ። ከሲኒማ ቤቱ ወጥተን ከጎኑ ወዳለው ህንጻ አቅጣጫ አመራን። ህንጻው ያለበት ቦታ የአንድ ጓደኛዬ ወላጆች ቤት እንደሆነ ትዝ ብሎኝ ነበር። በዚህ ጊዜ ጓደኞቼ፥ የዛች ጓደኛችን ቤት እና መሬት እንዳይወሰድ እና ይህ ህንጻ እንዳይገነባ ተቃውሞ አድርገው እንዳልተሳካላቸው ነግረውኝ ዘወር አሉ። እኔ ብቻዬን ቀስ እያልኩ በቀረብኩት ቁጥር ከፊት ለፊቱ የአንድ ኩባንያ ስም በእንግሊዝኛ እንደተጻፈ እየተገለጸልኝ ሄደ። ይህንን ሳይ በልቤ የሚሰማኝ፥ ድርጅቱ የአንድ ታዋቂ የአሜሪካ ኩባንያ ንብረት እንደሆነ ነው። ይህ ኩባንያ ደግሞ በአለም ላይ በተለይ ከነዳጅ ዘይት ጋር በተያያዘ ጥቅሙን ለማስከበር ሲል ጦርነት እስከማስጀመር ድረስ የማይገባበት ጉድጓድ እንደሌለ ይነገራል።

ህንጻው አጠገብ ስደርስ ታስሮ እንደቆየ ውሻ የተቆጡ ጠባቂዎች መቅረብ እንደማልችል ነገሩኝ። ማስጠንቀቂያቸውን ሳልቀበል እርምጃዬን ቀጠልኩ። ትኩር ብዬ እና በጉጉት ተሞልቼ የሚካሄደውን ነገር ለማስተዋል ተመለከትኩ። እየቀረብኩ በሄድኩ ቁጥር ከውስጥ የሚወጣ ጥቁር ጭስ እንዳለ ተመለከትኩ። ህንጻው እንደታሸገ እና ሰው እንዳይጠጋው እንደማይፈለግም ተረዳሁ። ከጠባቂዎቹ አንዱ ይሆን ማን እንደሆነ የማላስታውሰው ሰው፤ ኩባንያው ማእድን ሊያወጣ እንደመጣ፤ ከዛም ስራ ጋር በተያያዘ አንድ በአሜሪካን አገር የተከለከለ የሳይንስ ሙከራ አድርጎ አደገኛ ውጤት እንዳገኘ እና በሙከራው ውጤት ያገኘውን ገዳይ ኬሚካል መቆጣጠር ተስኖት ህንጻውን እንዳሸገው ይነግረኛል። ወዲያውኑም ጠባቂዎቹ በጉልበት ይዘው ከስፍራው አስወገዱኝ።

ባየሁት ሁሉ ግራ ተጋብቼ ባለሁበት፣ አሁንም ማን እንደሆነ የማላውቀው ሰው የቪዲዮ ጉብኝት የሚሰጠኝ ይመስል ከተማዋን ሁሉ በአንድ ቦታ አድርጎ ያሳየኛል። "አየሽ፣ እድገት አለ...ብዙ እድገት...ከተማዋ ህንጻ በህንጻ ነች። ግን ጥሩ እድገት አይደለም። የወያኔዎቹ እድገት ጥሩ እድገት አይደለም። ቶሎ ብለሽ ለጓደኞችሽ ንገሪያቸው። አበክረሽ ንገሪያቸው። ይህ የሆነው ከሃያ አመት በኋላ ነው። ግን አሁኑኑ፣ ይህ የወያኔ አይነት እድገት ሳይመጣ በፊት፤ አገሪቱ ከመወረሯ በፊት እንዲያስቆሙት ለጓደኞችሽ ንገሪያቸው። የሆነውን ነገር በህልሜ አይቼዋለሁ ብለሽ አስረጂያቸው። ጊዜ የለም በያቸው" ይለኛል።

ይህ ደምጽ ደግሞ ደጋግሞ፥ "አበክረሽ አስረጂያቸው። በደንም አስረጂያቸው።" ይለኛል። ከዛ በኋላ እኔም ነቃሁ፤ ድምጹም ሄደ። እንደዚህ ያለ ጥርት ያለ ህልም ካየሁ ረዥም ጊዜ ሆኖኛል።

ይህ የባልደረባዬ ህልም ነው። ፈጠራ አይደለም። ህልም ከፈጠራ ስራዎች ተርታ ይመደብ ካልሆነ በስተቀር።

ህልሙን ለፈቺው ትተነዋል። አጭር አስተያየት ግን መስጠት እንፈልጋለን።

በርግጥ፥ ከዚህ ህልም በመነሳት ከውጭ ከሚታየው ባሻገር ውስጡ ቀፎ ስለሆነው የወያኔ የእድገት ፕሮፓጋንዳ እና በያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አእምሮ ላይ ስላለው ሰፊሩን፣ አገሩን እና ንብረቱን የማጣት ስጋት ብዙ ልንል እንችላለን። ዛሬ በአንድ ነገር ላይ እናተኩር።

ዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ አስፈሪ በሆነ ፍጥነት የኢትዮጵያን መሬት ለባዳ አገር ነጋዴዎች አሳልፎ እየሰጠ ያለበት አንድ ምክንያት፤ እነዚህን ጉልበተኛ አለማቀፍ ኩባንያዎች የራሱ ደጋፊዎች ለማድረግ ነው። ኩባንያዎቹ መሬት ወስደው በአስርተ ሚሊዮን የሚቆጠር መዋለ ንዋይ ካፈሰሱበት በኋላ፣ በንግድ ጥቅማቸው ላይ አደጋ ይፈጥርብናል ብለው የሚያስቡትን ነገር ሁሉ ከምድረ-ገጽ ለማጥፋት ከመስራት ወደኋላ አይሉም። ከአደጋዎቹ አንዱ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ እራሱ ከሆነ፣ እሱም ለዘላለም ባሪያ ሆኖ እንዲኖር፣ አስፈላጊ ከሆነም እንዲጨፈጨፍ ከመርዳት ወደ ኋላ አይሉም።

አገዛዙ በአሁኑ ሰዓት ለብዙዎቹ የባዳ አገር ነጋዴዎች ከግብር ነጻ የሆነ ድልድል እያደረገ ነው። እንዲህ አይነቱ ጥቅም ደግሞ የመንግስት ለውጥ ቢኖር ሊቆም የሚችል ነው። ስለዚህ እነዚህ ነጋዴዎች የኢትዮጵያን ህዝብ የመንግስት ለውጥ ጥማት አይጋሩም፤ እንዳውም እንዳይከሰት ይሰራሉ።

ይህ ብቻ አይደለም፤ እነዚህ ጉልበተኛ ኩባንያዎች፣ ዴሞክራሲያዊ በሚባሉት የምእራብ አገራት ጨምሮ በየአገሮቻቸው ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ተጽእኖ አላቸው። ስለዚህ መንግስታቶቻቸው ወያኔ ህዝብ ሲያርድ እና ሲዘርፍ ዝም እንዲሉ ሊያስደርጉ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ የምእራብ አገር መንግስታት ነፍሰ ገዳይ አምባገነኖችን ዝም ብለው የሚደግፉትም ጉልበተኛ ነጋዴዎቻቸው በዛ አገር ጥቅም ስላላቸው ነው።

በአለማቀፍ ጉልበተኛ ነጋዴዎች ምክንያት ከዚህ ቀደም ህዝብ የመረጣቸው መንግስታት ተገልብጠዋል፤ የእርስ በርስ ጦርነት እንዲነሳ ተደርጓል፤ ብዙ ታሪክ ብቻ የሚነግረው ወንጀል ተፈጽሟል።

ዛሬ አገራችን የተጋፈጠችው አደጋ ይህ ነው። ይህንን ችግር ደግሞ እኛም በጉብዝናችን ወራት፤ ችግሩም ስር ሳይሰድ እና ከቁጥጥራችን ውጪ ሳይወጣ ካላቆምነው፤ ነገ በገዛ አገራችን ፈላጭ ቆራጮቹ የዘረኞቹ ልጆች እና ጉልበተኛ የባዳ አገር ነጋዴዎች ሆነው፤ እኛ ባይተዋር እንደምንሆን ግልጽ ነው። እነሱ ሲፈነጩብን፣ እኛ ፈገግታችን ከፊታችን ጠፍቶ፣ አንገታችንን ደፍተን የነሱ ሎሌዎች መሆናችን ላይቀር ነው።

**ወገኔ ሆይ! አገር የማዳን ቀን ዛሬ ነው።**

### የአባ ዱላ ገመዳ የቀኝ እጅ የምትባል መሃንዲስ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ምንጮቻችን እንደሚሉት፥ በግለሰቧ መኖሪያ ቤት ላይ በተደረገው ፍተሻ ሮቶ በተባለው የውሃ ማጠራቀሚያ ጋን ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው ጥሬ ብር ተከምሮ ተገኝቷል። ጉዳዩ፥ ይህች የአንዲት ትንሽ ከተማ ዝቅተኛ ባለስልጣን ይህን ያህል ገንዘብ ከሰበሰበች፣ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉት ደግሞ ምን ያህል ደብቀዋል የሚል ጥያቄ ጭሯል።

ቤታቸው ከተፈተሸው ሌሎች የከተማዋ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣናት ውስጥ አንዳንዶቹም በግቢያቸው ውስጥ ትላልቅ የመንግስት ወይም የንግድ ተቋማት እንደሚያደርጉት የጥበቃ ካሜራዎች አስተክለው እንደተገኙ ለማወቅ ተችሏል።

## በትግራዩ ገዢ ጉጅሌ አገዛዝ ስር የኢትዮጵያ ህዝብ እሮሮ እየተባባሰ ሄዷል

በትግራዩ ገዢ ጉጅሌ አገዛዝ ስር የኢትዮጵያ ህዝብ እሮሮ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ ሄዶ በቁጣ የሚፈነዳበት ጫፍ ላይ እየደረሰ መሆኑን ከአገሪቱ ዙሪያ የደረሱን ዘገባዎች አመልክተዋል።

ሪፖርተሮቻችን በአገሪቱ ዙሪያ የሚገኙ ነዋሪዎችን አነጋግረው የላኩልን ዘገባ እንደሚያመለክተው፣ ከአዲስ አበባ እስከ አዳማ፣ ከባህር ዳር እስከ መቱ እና ጅማ ያሉ ኢትዮጵያውያን በልቅሶ ከተቀላቀለ ምሬት በስተቀር የሚገልጹት የላቸውም። በአዲስ አበባ፥ ህዝቡ በዋነኛነት ስለ ኑሮ ውድነት እና ስለ ሙስና፤ ቀጥሎም ስለ ውሃ እና ስለመብራት እጥረት፤ እንዲሁም ስለ ትራንስፖርት ችግር ያማርራል።

በመዲናይቱ ዘጋቢያችን በጥቆማ ያገኛቸው አንድ ግለሰብ፣ ንጹህ ልብስ ለብሰው ወደ ምሽት አካባቢ ላይ መንገድ ዳር በመቆም ይለምናሉ። ግለሰቡ በተለምዶ በልመና ስራ ከሚሰማሩ ሰዎች በአለባበሳቸውም ሆነ በአኳኋናቸው መለየታቸው መጀመሪያ ላይ ግራ ያጋባል። ሚስጥሩ የሚገለጠው ግን ጠጋ ብሎ ላናገራቸው ነው።

"ሃፍረት ድሮ ቀረ" በማለት በስቃያቸው ላይ የሚቀልዱት እኒህ ጎልማሳ፣ የመንግስት ሰራተኛ መሆናቸውን እና ቤተሰባቸውን በደሞዛቸው ማስተዳደር ስለተሳናቸው እራሳቸውን በልመና መደጎም መጀመራቸውን ያስረዳሉ። በርግጥ የመንግስት ሰራተኞች ለልመና መውጣት አዲስ ነገር ቢሆንም፤ በአዲስ አበባ ከተማ ባሉ ብዙ ቤተሰቦች ውስጥ ምግብ በፈረቃ መብላት ከተጀመረ መቆየቱን ከዚህ ቀደም ገልጸናል። አንዲት የተባበሩት መንግስታት የምግብ ፕሮግራም ሰራተኛም ይህንኑ ሃቅ መመስከራቸው ይታወሳል።

በምእራብ ኢትዮጵያ ባለች አንዲት ትንሽ ከተማ ሪፖርተራችንን ያናገሩት አንድ አዛውንት ደግሞ፥ "መብራት እና ውሃ ቢመጡም ቢቀሩ ጉዳይ የለንም፤ እኛ ድሮውንም ኩራዝ ማብራት እና ከወንዝ መቅዳት ለምደናል" ይላሉ። በሳቸው ከተማ ህዝቡን ለበሽታ እየዳረገው ያለው ግን የኑሮ ውድነት ነው። "መቶ ብር ተይዞ ገበያ ተኪዶ የአንድ ዘንቢል ግማሽ የማይሆን ነገር ተገዝቶ ይመጣል። እንኳን ደሞዝ የሌለን ሽማግሎች፤ የመንግስት ሰራተኞቹም መግቢያ አጥተዋል" ብለዋል። የሰባ አራት አመቱ አዛውንት የሚጠራቸው ቢያገኙ ጫካ ገብተው የትግራዩን ገዢ ጉጅሌ ለመዋጋት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በጅማ፣ በባህር ዳር እና በአዳማም ተመሳሳይ ለቅሶ ተሰምቷል። የዘረኛው ቡድን አገልጋዮች የሆኑ ጥቂቶች ከአገዛዙ ጋር ተመሳጥረው ባጋበሱት፣ ወይም ቀጥታ ከህዝብ በዘረፉት ገንዘብ የቅንጦት ኑሮ ሲኖሩ፤ ብዙሃኑ በረሃብና በእርዛት እየተሸማቀቁ ነው። ዘጋቢዎቻችን በሄዱባቸው ቦታዎች ሁሉ ለማወቅ እንደቻሉት፤ ህዝቡ ለሚደርስበት መከራ ሁሉ በዋናኛነት ተጠያቂው ስልጣንን በጉልበት ተቆጣጥሮ ያለው ዘረኛ አገዛዝ እና በዘረፋው የሚያግዙት የየመንደሩ ካድሬዎች መሆናቸውን ጠንቅቆ ተረድቷል። በአዳማ ነዋሪ የሆኑ አንዲት እናት ለዘጋቢያችን እንደተናገሩት፣ አንዲት ክር ብትጎተት እሳቸውን ጨምሮ በቁጣ እና በምሬት የተሞላው ህዝብ ሆ ብሎ ለመውጣት እና ለማመጽ፣ በገዢዎቹም ላይ የበቀል እርምጃን ለመውሰድ ዝግጁ ነው ብለዋል።

## የዘረኛው አገዛዝ ዘረፋ የሰሞኑ ተረኞች እድሮች መሆናቸው ተዘገበ

ከህዝብ ጉሮሮ በመንጠቅ ኪሳቸውን ሲጠቀጥቁ የቆዩት የትግራዩ ገዢ ቡድን ባለስልጣናት አሁንም ዘረፋቸውን የሚያበዙበትን መንገድ እየቀየሱ እንደሆነና ቀጣይ ተረኞች እድሮች መሆናቸውን አዲስ ነገር ኦንላይን የተባለው የዜና ድረ-ገጽ ዘግቧል።

እንደ ድረ-ገጹ ዘገባ፥ በጉጅሌው ሹመኞች የተሞላው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የመዲናይቱ እድሮች ለእድገትና ትራንስፎርሜሽን ተብዬው አዲስ የዘረፋ ሰበብ የገንዘብ ስጦታ እንዲያበረክቱ ግዳጅ ጥሏል። እድሮቹ መስተዳደሩ ላወጣው የአምስት አመት እቅድ የበኩላቸውን እንዲያዋጡ በሚል ኮታ እንደተጣለባቸው ዘገባው አመልክቷል።

በዚህም አኳኋን ማህበራቱ በተለያየ እርከን ተደርድረው እያንዳንዳቸው ከአምስት መቶ ብር እስከ አምስት ሺህ ብር ድረስ እንዲከፍሉ ተወስኖባቸዋል። እነሱ ደግሞ በተራቸው አባላቶቻቸውን በመሰብሰብ ይህንን ግዳጅ በመወጣታቸው የሚፈጠርባቸውን ጉድለት ለማካካስ ድግሞ እንዲያደርጉላቸው ጠይቀዋል።

ዘረኛው አገዛዝ አቅሙን ከግምት ሳያስገባ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ እና ለምርጥ ዘር ባለስልጣናቱ የሙስና እድል ለመፍጠር ሲል ያወጣውን የአምስት አመት እቅድ ከግብ ለማድረስ በሚል ህዝቡን መበዝበዝ እንደጀመረ ይታወቃል። ማህበራት እና ግለሰቦች በንግድ ባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ ጫና በማድረግ ላይ ሲሆን፤ በቅርቡም የትሬዠሪ ቦንድ በግዳጅ የመሸጥ እቅድ እንደያዘ መገለጹ ይታወሳል። አገዛዙ ከዚህ ሁሉ በተጨማሪም ከውጭ አገራት ባንኮች እና የገንዘብ ተቋማት በአገሪቱ ስም ብድር እና እርዳታ ይወስዳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፥ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገራት ባንኮች የሚፈልሰው ገንዘብ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ሲሆን፤ ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ እና ባለቤቱ ከቢሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት ገንዘብ በውጭ አገራት ባንኮች ደብቀው እንደሚገኙ አንዳንድ የዜና ምንጮች ይናገራሉ። ከሶስት አመታት በፊት የአገሪቱ ኦዲተር ጄኔራል ከ7.2 ቢሊዮን ብር በላይ ከአገሪቱ በጀት ውስጥ የት እንደገባ እንደማይታወቅ በማጋለጣቸው ከስራቸው መባረራቸው በዘረኛው አምባገነን ሰው መተካታቸው ይታወሳል።

## በአገራቸው የሚካሄደውን ሰቆቃ ለመቃወም ኢትዮጵያውያን የጀመሩት የፊርማ ማሰባሰቢያ ዘመቻ በወያኔ ጥቃት ተደረገበት

በርካታ ንጹሃን ዜጎች በትግራዩ ገዢ ጉጅሌ እስር ቤቶች ውስጥ እየደረሰባቸው ያለውን ሰቆቃ በማጋለጥ በቅርቡ የወጣውን ሪፖርት ተከትሎ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ፕሮጀችት የተሰኘ ቡድን የጀመረው የፊርማ ማሰባሰብ ዘመቻ በአገዛዙ ጥቃት ተፈጽሞበታል።

ለፕሮጀክቱ ቅርብ የሆኑ ምንጭ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፥ ኢትዮጵያውያኑ በዜጎች ላይ የሚፈጸመውን ሰቆቃ በመቃወም ኮሚቴ አጌነስት ቶርቸር ለተባለው የተባበሩት መንግስታት አካል የሚደርስ የኢንተርኔት የፊርማ ማሰባሰቢያ ዘመቻ ጀምረዋል። ይሁን እንጂ፥ እንቅስቃሴው መተዋወቅ እንደጀመረ የዘረኛው አገዛዝ ቅጥረኞች ፊርማው በሚሰበሰብበት ድረ-ገጽ ላይ የሳይበር ጥቃት ከፍተዋል። ምንጫችን ከላኩልን ደጋፊ ማስረጃ መረዳት እንደቻልነው፥ የጥቃቱ ፈጻሚዎች በአንድ ጊዜ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተመሳሳይ ፊርማዎች በማስገባት ለማስተጓጎል ሞክረዋል።

የፕሮጀክቱ አስተባባሪዎች ይህንን ለመከላከል የሚያችላቸውን ዘዴ በመቀየስ የፊርማ ማሰባሰቢያ ጣቢያቸውን ወደ ሌላ ድረ-ገጽ አዛውረዋል። አዲሱ ጣቢያ thepetitionsite.com በሚባለው ድረ-ገጽ ላይ የሚገኝ ሲሆን ethiopianhu-manrights.org የሚለውን ቃል በመፈለግ ሊገኝ ይችላል።

የጋዜጣ ዝግጂት ክፍላችን ሬድዮ ኢንተርኔት ማግኘት የሚችሉ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በዚህ ቅጽ ላይ በመፈረም የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በአገራቸው የሚፈጽመውን አረመኔያዊ ተግባር እንዲቃወሙ እና ለወዳጅ ዘመዶቻቸውም እንዲያስታውቁ ያበረታታል።

## በትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ጥቃት የተከፈተበት የንግድ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የተወሰኑ አጭበርባሪ ነጋዴዎች ቢኖሩም፤ የሚያጭበረብሩት ብቻቸውን ሳይሆን፤ በአገዛዙ ውስጥ ባሉ ሰዎች እርዳታ ነው ብለዋል።

ባሁኑ ሰዓት የንግዱን ማህበረሰብ በሚመለከት የሚወጡት ህጎች ብዙ ክፍተቶች እንዳሉት እና የዛሬ አመት በሆኑ ነገሮች ላይ ዛሬ በወጣ ህግ ሃጢያተኛ ይኮናል ሲሉ አማረዋል።

ነጋዴዎች እቃ በመደበቅ የዋጋ ንረት እየፈጠሩ ነው የሚለውን የአገዛዙን ክስ ያጣጣሉት አቶ እየሱስ ወርቅ፤ እንደ ኢትዮጵያ ባለች አገር፣ ከአገዛዙ በሚደርግላቸው እርዳታ ለመሽሎክሎክ ከሚችሉት በስተቀር፣ በአንድ ምርት የገበያ ዋጋ ላይ ተጽእኖ ማድረግ የሚችል ትልቅ ነጋዴ የለም ይላሉ። እንደ ጅንአድ ያሉ እና በአገዛዙ ቁጥጥር ስር የሚገኙ የመንግስት ተቋማት ግን እንደዚህ ባሉ ተግባራት እንደሚሳተፉ አስረድተው፤ እነሱ እያሉ ሌሎች ነጋዴዎችን መቅጣት አህያውን ትቶ ዳውላውን አይነት ነው ሲሉ ተርተዋል።

እንደ መሬት ካለ ጉዳይ ጋርም በተያያዘ በንግዱ ማህበረሰብ ላይ ስላንዣበበው ስጋት ስሞታ ያሰሙት ታዋቂ ነጋዴ፤ "እኔ በእውነት ምርር ብሎኝ ነው ዛሬ የምናገረው::" ብለዋል።

ማህበረሰቡ ውስጥ ከተፈጠረው ስጋት የተነሳ በርካታ ነጋዴዎች ከአገር መውጣታቸውን ፎርቹን የተባለውን የእንግሊዝኛ ጋዜጣ መዘገቡ ይታወሳል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org